# Isa

## Chapter 22

### Amharic Interlinear

Reference: Amharic Selassie Bible

1

| Hebrew | Amharic | Strong's |
|---|---|---|
| מַשָּׂא | መሻ-የ | |
| גֵּיא | ሸለቆ-የ | H1516 |
| חִזָּיוֹן | ራእይ | H2384 |
| מַה־ | ምን- | H4100 |
| לָּךְ | -ለ-አንቺ | |
| אֵפוֹא | እንግዲህ | H0645 |
| כִּי־ | ስለ- | |
| עָלִית | ወጣሽ | H5927 |
| כֻּלָּךְ | ሁሉ-የሽ | H3605 |
| לַגַּגּוֹת׃ | -ለ-ያን-ጣሪያዎች | H1406 |

> ስለ ራእይ ሸለቆ የተነገረ ሸክም። እናንተ ሁላችሁ ወደ ሰገነት መውጣታችሁ ምን ሆናችኋል?

2

| Hebrew | Amharic | Strong's |
|---|---|---|
| תְּשֻׁאוֹת | ጩኸቶች | H8663 |
| מְלֵאָה | የሞላ-ው | H4395 |
| עִיר | ከተማ | |
| הוֹמִיָּה | ጩኺ-ው | H1993 |
| קִרְיָה | ከተማ | H7151 |
| עַלִּיזָה | ደስተኛ-ው | H5947 |
| חֲלָלַיִךְ | ተገደሎች-የሽ | |
| לֹא | አይደሉም | H3808 |
| חַלְלֵי־ | ተገደሎች-የ | |
| חֶרֶב | ሰይፍ | H2719 |
| וְלֹא | -እና-አይደሉም | H3808 |
| מֵתֵי | ሙቶች-የ | H4191 |
| מִלְחָמָה׃ | ጦርነት | H4421 |

> ጩኸትና ፍጅት የተሞላብሽ ከተማ፥ ደስታ ያለሽ ከተማ ሆይ፥ በአንቺ ውስጥ የተገደሉት በሰይፍ የተገደሉ አይደሉም፥ በሰልፍም የሞቱ አይደሉም።

3

| Hebrew | Amharic | Strong's |
|---|---|---|
| כָּל־ | ሁሉ-የ | H3605 |
| קְצִינַיִךְ | መሪዎች-የሽ | H7101 |
| נָדְדוּ־ | ሸሹ- | H5074 |
| יַחַד | አንድ-ላይ | |
| מִקֶּשֶׁת | -ከ-ቀስት | H7198 |
| אֻסָּרוּ | ታሰሩ | H0631 |
| כָּל־ | ሁሉ-የ | H3605 |
| נִמְצָאַיִךְ | የተገኙ-የሽ | H4672 |
| אֻסְּרוּ | ታሰሩ | H0631 |
| יַחְדָּו | አንድ-ላይ | |
| מֵרָחוֹק | -ከ-ሩቅ | H7350 |
| בָּרָחוּ׃ | ሸሹ | H1272 |

> አለቆችሽ ሁሉ በአንድነት ሸሹ፥ ያለ ቀስትም ተማረኩ፤ ከሩቅ ሸሽተው ከአንቺ ዘንድ የተገኙት ሁሉ በአንድነት ታሰሩ።

4

| Hebrew | Amharic | Strong's |
|---|---|---|
| עַל־ | -በ- | |
| כֵּן | እንዲህ | |
| אָמַרְתִּי | አልሁ | H0559 |
| שְׁעוּ | ዘወር-በሉ | H8159 |
| מִנִּי | -ከ-እኔ | |
| אֲמָרֵר | ማረር | H4843 |
| בַּבֶּכִי | -በ-ያን-ለቅሶ | H1065 |
| אַל־ | አል- | H0408 |
| תָּאִיצוּ | ትፋጠኑ | H0213 |
| לְנַחֲמֵנִי | -ለ-ማጽናናት-እኔን | H5162 |
| עַל־ | -በ- | |
| שֹׁד | ጥፋት-የ | H7701 |
| בַּת־ | ሴት-ልጅ-የ | H1323 |
| עַמִּי׃ | ሕዝቤ-የ | |

> ስለዚህ። ፊታችሁን ከእኔ ዘንድ አርቁ፤ መራራ ልቅሶ አለቅሳለሁ፤ ስለ ሕዝቤ ሴት ልጅ ጥፋት ታጽናኑኝ ዘንድ አትድከሙ አልሁ።

5

| Hebrew | Amharic | Strong's |
|---|---|---|
| כִּי | ስለ | |
| יוֹם | ቀን-የ | H3117 |
| מְהוּמָה | ሁካታ | H4103 |
| וּמְבוּסָה | -እና-ረገጣ | H4001 |
| וּמְבוּכָה | -እና-ግራ-መጋባት | H3998 |
| לַאדֹנָי | -ለ-ጌታ | H0136 |
| יְהוִה | እግዚአብሔር | H3069 |
| צְבָאוֹת | ሰባኦት | |
| בְּגֵיא | -በ-ሸለቆ-የ | H1516 |
| חִזָּיוֹן | ራእይ | H2384 |
| מְקַרְקַר | የሚያፈርስ | |
| קִר | ቅጥር | H7023 |
| וְשׁוֹעַ | -እና-ጩኸት | |
| אֶל־ | -ወደ- | H0413 |
| הָהָר׃ | -ያን-ተራራ | H2022 |

> ከሠራዊት ጌታ ከእግዚአብሔር ዘንድ የድንጋጤና የመረገጥ የድብልቅልቅም ቀን፥ የቅጥርም መፍረስ ወደ ተራራም መጮኽ በራእይ ሸለቆ ውስጥ ሆኖአል።

6

| Hebrew | Amharic | Strong's |
|---|---|---|
| וְעֵילָם | -እና-ዔላም | |
| נָשָׂא | አነሣ | H5375 |
| אַשְׁפָּה | የፍላጻ-ከረጢት | H0827 |
| בְּרֶכֶב | -በ-ሰረገላ | H7393 |
| אָדָם | ሰው | H0120 |
| פָּרָשִׁים | ፈረሰኞች | |
| וְקִיר | -እና-ቂር | |
| עֵרָה | አራቆተ | H6168 |
| מָגֵן׃ | ጋሻ | H4043 |

> ኤላምም ከሰረገለኞችና ከፈረሰኞች ጋር ሆኖ አፎቱን ተሸከመ፥ ቂርም ጋሻውን ገለጠ።

7

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| וַיְהִי | מִבְחַר־ | עֲמָקַיִךְ | מָלְאוּ | רָכֶב | וְהַפָּרָשִׁים | שֹׁת | שָׁתוּ | הַשָּׁעְרָה: |
| -እና-ሆነ | ምርጥ-የ | ሸለቆዎች-የሸ | ሞሉ | ሰረገላ | -እና-ያን-ፈረሰኞች | ቆም-ቁም | ቆሙ | -ያን-በር-የ-ሸ |
| H1961 | H4005 | H6010 | H4390 | H7393 | | H7896 | H7896 | H8179 |

መልካሞቹንም ሸለቆችሽን ሰረገሎች ሞሉባቸው፥ ፈረሰኞችም መቆሚያቸውን በበር ላይ አደረጉ።

8

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| וַיְגַל | אֵת | מָסַךְ | יְהוּדָה | וַתַּבֵּט | בַּיּוֹם | הַהוּא | אֶל־ | נֶשֶׁק | בֵּית | הַיָּעַר: |
| -እና-ገለጠ | (ዓ.ም.) | መጋረጃ-የ | ይሁዳ | -እና-ተመለከትህ | -በ-ያቺ-ቀን | ያቺ | -ወደ- | መሣሪያ-የ | ቤት-የ | -ያን-ጫካ |
| H1540 | H0853 | H4539 | H3063 | H5027 | H3117 | H1931 | H0413 | H5402 | | |

የይሁዳንም መጋረጃ ገለጠ፤ በዚያም ቀን በዱር ቤት የነበረውን የጦር ዕቃ ተመለከትህ፥

9

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| וְאֵת | בְּקִיעֵי | עִיר־ | דָּוִד | רְאִיתֶם | כִּי־ | רָבּוּ | וַתְּקַבְּצוּ | אֶת־ | מֵי | הַבְּרֵכָה | הַתַּחְתּוֹנָה: |
| -እና-(ዓ.ም.) | ስንጥቆች-የ | ከተማ-የ | ዳዊት | አያችሁ | ስለ- | በዙ | -እና-ሰበሰባችሁ | (ዓ.ም.) | ውኃዎች-የ | -ያን-ገንዳ | -ያን-ታችኛ-ው |
| H0853 | H1233 | | H1732 | H7200 | | | H6908 | H0853 | H4325 | H1295 | H8481 |

የዳዊትም ከተማ ፍራሾች እንደ በዙ አይታችኋል፥ የታችኛውንም ኵሬ ውኃ አከማችታችኋል፥

10

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| וְאֶת־ | בָּתֵּי | יְרוּשָׁלִַם | סְפַרְתֶּם | וַתִּתְצוּ | הַבָּתִּים | לְבַצֵּר | הַחוֹמָה: |
| -እና-(ዓ.ም.) | ቤቶች-የ | ኢየሩሳሌም | ቆጠራችሁ | -እና-አፈረሳችሁ | -ያን-ቤቶች | -ለ-ማጠናከር | -ያን-ቅጥር |
| H0853 | | H3389 | | H5422 | | H1219 | H2346 |

የኢየሩሳሌምን ቤቶች ቈጠራችሁ ቅጥሩንም ለማጥናት ቤቶችን አፈረሳችሁ።

11

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| וּמִקְוָה | עֲשִׂיתֶם | בֵּין | הַחֹמֹתַיִם | לְמֵי | הַבְּרֵכָה | הַיְשָׁנָה | וְלֹא | הִבַּטְתֶּם | אֶל־ | עֹשֶׂיהָ | וְיֹצְרָהּ | מֵרָחוֹק | לֹא | רְאִיתֶם: |
| -እና-ማጠራቀሚያ | አደረጋችሁ | መካከል | -ያን-ቅጥሮች-ሁለቱ | -ለ-ውኃዎች-የ | -ያን-ገንዳ | -ያን-አሮጌ-ው | -እና-አልተመለከታችሁም | ተመለከታችሁ | -ወደ- | ሠሪ-የ-ው | -እና-ፈጣሪ-የ-ው | -ከ-ሩቅ | አላያችሁም | አያችሁ |
| H4724 | | H0996 | H2346 | H4325 | H1295 | H3465 | H3808 | H5027 | H0413 | | H3335 | H7350 | H3808 | H7200 |

በአሮጌው ኵሬ ላለው ውኃ በሁለቱ ቅጥር መካከል መከማቻ ሠራችሁ፤ ይህን ያደረገውን ግን አልተመለከታችሁም፥ ቀድሞ የሠራውንም አላያችሁም።

12

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| וַיִּקְרָא | אֲדֹנָי | יְהוִה | צְבָאוֹת | בַּיּוֹם | הַהוּא | לִבְכִי | וּלְמִסְפֵּד | וּלְקָרְחָה | וְלַחֲגֹר | שָׂק: |
| -እና-ጠራ | ጌታ | እግዚአብሔር | ሰባኦት | -በ-ያቺ-ቀን | ያቺ | -ለ-ለቅሶ | -እና-ለ-ዋይታ | -እና-ለ-ቀላቃል | -እና-ለ-መታጠቅ | ማቅ |
| H7121 | H0136 | H3069 | | H3117 | H1931 | H1065 | H4553 | H7144 | H2296 | H8242 |

በዚያም ቀን የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ወደ ልቅሶና ወደ ዋይታ ራስን ወደ መንጨትና ማቅንም ወደ መልበስ ጠራ።

13

| | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| וְהִנֵּה | שָׂשׂוֹן | וְשִׂמְחָה | הָרֹג | בָּקָר | וְשָׁחֹט | צֹאן | אָכֹל | בָּשָׂר | וְשָׁתוֹת | יָיִן | אָכוֹל | וְשָׁתוֹ | כִּי | מָחָר | נָמוּת: |
| -እና-እነሆ- | ደስታ | -እና-ሐሤት | ማረድ | ከብት | -እና-ማረድ | በግ | መብላት | ሥጋ | -እና-መጠጣት | ወይን | ብሉ | -እና-ጠጡ | ስለ | ነገ | እንሞታለን |
| H2009 | H8342 | H8057 | H2026 | H1241 | | H6629 | H0398 | H1320 | H8354 | H3196 | H0398 | H8354 | | H4279 | H4191 |

እነሆም፥ ሐሤትና ደስታ በሬውንና በጉንም ማረድ ሥጋንም መብላት የወይን ጠጅንም መጠጣት ሆነዋል፤ እናንተ። ነገ እንሞታለንና እንብላ እንጠጣ ብላችኋል።

14

| וְנִגְלָ֥ה | בְאָזְנָ֖י | יְהוָ֣ה | צְבָא֑וֹת | אִם־ | יְכֻפַּ֞ר | הֶעָוֺ֤ן | הַזֶּה֙ | לָכֶ֔ם | עַד־ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| -እና-ተገለጠ | -በ-ጆሮዎች-የቼ | እግዚአብሔር | ሰባኦት | እም- | ይስተሰርያል | -ያን-በደል-የ | -ይህ | -ለ-እናንተ | እስከ- |
| H1540 | H0241 | H3068 | | | | H5771 | H2088 | | H5704 |

| תְּמֻת֔וּן | אָמַ֖ר | אֲדֹנָ֥י | יְהוִ֖ה | צְבָאֽוֹת׃ | פ |
|---|---|---|---|---|---|
| ትሞታላችሁ | አለ | ጌታ | እግዚአብሔር | ሰባኦት | פ |
| H4191 | H0559 | H0136 | H3069 | | |

ይህም ነገር በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ጆሮ ተሰማ። እስክትሞቱ ድረስ ይህ በደል በእውነት አይሰረይላችሁም ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።

15

| כֹּ֥ה | אָמַ֛ר | אֲדֹנָ֥י | יְהוִ֖ה | צְבָא֑וֹת | לֶךְ־ | בֹּא֙ | אֶל־ | הַסֹּכֵ֣ן | הַזֶּ֔ה | עַל־ | שֶׁבְנָ֖א |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| እንዲህ | አለ | ጌታ | እግዚአብሔር | ሰባኦት | ሂድ- | ግባ | -ወደ- | -ያን-ጠባቂ | -ይህ | -በ- | ሸብና |
| H3541 | H0559 | H0136 | H3069 | | H3212 | H0935 | H0413 | H5532 | H2088 | | H7644 |

| אֲשֶׁ֥ר | עַל־ | הַבָּֽיִת׃ |
|---|---|---|
| የ- | -በ- | -ያን-ቤት |

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። በቤቱ ውስጥ ወደ ተሾመው ወደዚህ አዛዥ ወደ ሳምናስ ሂድ እንዲህም በለው።

16

| מַה־ | לְּךָ֥ | פֹה֙ | וּמִ֣י | לְךָ֣ | פֹ֔ה | כִּֽי־ | חָצַ֧בְתָּ | לְּךָ֛ | פֹּ֖ה | קָ֑בֶר | חֹצְבִ֤י |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ምን- | -ለ-አንተ | እዚህ | -እና-ማን | -ለ-አንተ | እዚህ | ስለ- | ቀረጽክ | -ለ-አንተ | እዚህ | መቃብር | ቃረጪ-የ |
| H4100 | | H6311 | H4310 | | H6311 | | H2672 | | H6311 | H6913 | H2672 |

| מָרוֹם֙ | קִבְר֔וֹ | חֹקְקִ֥י | בַסֶּ֖לַע | מִשְׁכָּ֥ן | לֽוֹ׃ |
|---|---|---|---|---|---|
| ከፍታ | መቃብር-የ-ሩ | ቃቃሪ-የ | -በ-ያን-ዐለት | ማደሪያ | -ለ-እሱ |
| H4791 | H6913 | H2710 | H5553 | H4908 | |

መቃብር በዚህ ያስወቀርህ ከፍ ባለው ስፍራ መቃብር ያሰራህ በድንጋይም ውስጥ ለራስህ መኖርያ ያሳነጽህ በዚህ ምን አለህ? በዚህስ በአንተ ዘንድ ማን አለ?

17

| הִנֵּ֤ה | יְהוָה֙ | מְטַלְטֶלְךָ֔ | טַלְטֵלָ֖ה | גָּ֑בֶר | וְעֹטְךָ֖ | עָטֹֽה׃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| እነሆ | እግዚአብሔር | ወርዋሪ-የ-ህ | ወርወራ | ሰው | -እና-ጠቀለለ-የ-ህ | መጠቅለል |
| H2009 | H3068 | H2904 | H2925 | H1397 | | |

እነሆ፥ እግዚአብሔር በኃይል ወርውሮ ይጥልሃል፥ አጠንክሮም ይጨብጥሃል።

18

| צָנ֤וֹף | יִצְנָֽפְךָ֙ | צְנֵפָ֔ה | כַּדּ֕וּר | אֶל־ | אֶ֖רֶץ | רַחֲבַ֣ת | יָדָ֑יִם | שָׁ֣מָּה | תָ֗מוּת |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ጠቅልሎ | ይጠቅልልሃል | ጠቅል | -እንደ-ያን-ኳስ | -ወደ- | ምድር | ሰፊ-ው | እጆች | ወደ-እዚያ | ትሞታለህ |
| H6801 | H6801 | H6802 | | H0413 | H0776 | H7342 | H3027 | H8033 | H4191 |

| וְשָׁ֙מָּה֙ | מַרְכְּב֣וֹת | כְּבוֹדֶ֔ךָ | קְל֖וֹן | בֵּ֥ית | אֲדֹנֶֽיךָ׃ |
|---|---|---|---|---|---|
| -እና-ወደ-እዚያ | ሰረገላዎች-የ | ክብር-የ-ህ | ውርደት-የ | ቤት-የ | ጌቶች-የ-ህ |
| H8033 | H4818 | H3519 | H7036 | | H0113 |

ጠቅልሎም ያንከባልልሃል ወደ ሰፊይቱም ምድር እንደ ኳስ ይጥልሃል፤ አንተ የጌታህ ቤት እፍረት፤ በዚያ ትሞታለህ በዚያም የክብርህ ሰረገላዎች ይሆናሉ።

19

| וַהֲדַפְתִּ֖יךָ | מִמַּצָּבֶ֑ךָ | וּמִמַּעֲמָדְךָ֖ | יֶהֶרְסֶֽךָ׃ |
|---|---|---|---|
| -እና-እገፍሃለሁ | -ከ-ስፍራ-የ-ህ | -እና-ከ-ቦታ-የ-ህ | ይጥልሃል |
| H1920 | H4673 | H4612 | H2040 |

ከአዛዥነት ሥራህ አሳድድሃለሁ፥ ከሹመትህም ትሻራለህ።

20

| וְהָיָ֖ה | בַּיּ֣וֹם | הַה֑וּא | וְקָרָ֙אתִי֙ | לְעַבְדִּ֔י | לְאֶלְיָקִ֖ים | בֶּן־ | חִלְקִיָּֽהוּ׃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| -እና-ይሆናል | -በ-ያቼ-ቀን | ያቼ | -እና-እጠራለሁ | -ለ-አገልጋዮ-የቼ | -ለ-ኤልያቄም | ልጅ-የ | ሒልቅያሁ |
| H1961 | H3117 | H1931 | H7121 | H5650 | H0471 | | H2518 |

በዚያም ቀን ባሪያዬን የኬልቅያስን ልጅ ኤልያቄምን እጠራለሁ፥

21

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| וְהִלְבַּשְׁתִּיו | כֻּתָּנְתֶּךָ | וְאַבְנֵטְךָ | אֲחַזְּקֶנּוּ | וּמֶמְשַׁלְתְּךָ | אֶתֵּן | בְיָדוֹ | וְהָיָה |
| -እና-አለብሰዋለሁ | ካባ-የ-ህን | -እና-ቀበቶ-የ-ህን | አጠነክረዋለሁ | -እና-ግዛት-የ-ህን | እሰጣለሁ | -በ-እጅ-የ-ሩ | -እና-ይሆናል |
| H3847 | H3801 | H0073 | H2388 | H4475 | H5414 | H3027 | H1961 |
| לְאָב | לְיוֹשֵׁב | יְרוּשָׁלִַם | וּלְבֵית | יְהוּדָה׃ | | | |
| -ለ-አባት | -ለ-ነዋሪ-የ | ኢየሩሳሌም | -እና-ለ-ቤት-የ | ይሁዳ | | | |
| H0001 | H3427 | H3389 | | H3063 | | | |

> መጐናጸፊያህንም አለብሰዋለሁ፥ በመታጠቂያህም አስታጥቀዋለሁ፥ ሹመትህንም በእጁ አሳልፌ እሰጠዋለሁ፤ በኢየሩሳሌምም ለሚኖሩ ለይሁዳም ቤት አባት ይሆናል።

22

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| וְנָתַתִּי | מַפְתֵּחַ | בֵּית־ | דָּוִד | עַל־ | שִׁכְמוֹ | וּפָתַח | וְאֵין | סֹגֵר | וְסָגַר |
| -እና-እሰጣለሁ | ቁልፍ-የ | ቤት-የ | ዳዊት | -በ- | ትከሻ-የ-ሩ | -እና-ይከፍታል | -እና-የለም | ዘጋ-ው | -እና-ይዘጋል |
| H5414 | H4668 | | H1732 | | H7926 | | H0369 | H5462 | H5462 |
| וְאֵין | פֹּתֵחַ׃ | | | | | | | | |
| -እና-የለም | ከፋች | | | | | | | | |
| H0369 | | | | | | | | | |

> የዳዊትንም ቤት መክፈቻ በጫንቃው ላይ አኖራለሁ፤ እርሱም ይከፍታል የሚዘጋም የለም እርሱም ይዘጋል የሚከፍትም የለም።

23

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| וּתְקַעְתִּיו | יָתֵד | בְּמָקוֹם | נֶאֱמָן | וְהָיָה | לְכִסֵּא | כָבוֹד | לְבֵית | אָבִיו׃ |
| -እና-እሰካዋለሁ | ምስማር | -በ-ቦታ | ታማኝ | -እና-ይሆናል | -ለ-ዙፋን-የ | ክብር | -ለ-ቤት-የ | አባት-የ-ሩ |
| H8628 | H3489 | H4725 | H0539 | H1961 | H3678 | H3519 | | H0001 |

> በታመነም ስፍራ እንደ ችንካር እተክለዋለሁ፥ ለአባቱም ቤት የክብር ዙፋን ይሆናል።

24

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| וְתָלוּ | עָלָיו | וְכֹל | כְּבוֹד | בֵּית־ | אָבִיו | הַצֶּאֱצָאִים | וְהַצְּפִעוֹת | כֹּל | כְּלֵי |
| -እና-ይሰቅሉ | -በ-እሱ-ላይ | ሁሉ-የ | ክብር-የ | ቤት-የ | አባት-የ-ሩ | -ያን-ዘሮች | -እና-ያን-ቡቃያዎች | ሁሉ-የ | ዕቃዎች-የ |
| H8518 | | H3605 | H3519 | | H0001 | H6631 | H6849 | H3605 | H3627 |
| הַקָּטָן | מִכְּלֵי | הָאַגָּנוֹת | וְעַד | כָּל־ | כְּלֵי | הַנְּבָלִים׃ | | | |
| -ያን-ትንሹ | -ከ-ዕቃዎች-የ | -ያን-ጽዋዎች | -እና-እስከ | ሁሉ-የ | ዕቃዎች-የ | -ያን-ጋኖች | | | |
| | H3627 | H0101 | H5704 | H3605 | H3627 | | | | |

> የአባቱንም ቤት ክብር ሁሉ ልጆቹንም የልጅ ልጆቹንም፥ ከጽዋ ዕቃ ጀምሮ እስከ ማድጋ ዕቃ ድረስ፥ ታናናሹን ዕቃ ሁሉ ይሰቅሉበታል።

25

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| בַּיּוֹם | הַהוּא | נְאֻם | יְהוָה | צְבָאוֹת | תָּמוּשׁ | הַיָּתֵד | הַתְּקוּעָה | בְּמָקוֹם | נֶאֱמָן |
| -በ-ያቺ-ቀን | ያቺ | የሚል-የ | እግዚአብሔር | ሰባኦት | ትፈናቀላለች | -ያን-ምስማር | -ያን-የተሰካ-ው | -በ-ቦታ | ታማኝ |
| H3117 | H1931 | H5002 | H3068 | | H4185 | H3489 | H8628 | H4725 | H0539 |
| וְנִגְדְּעָה | וְנָפְלָה | וְנִכְרַת | הַמַּשָּׂא | אֲשֶׁר־ | עָלֶיהָ | כִּי | יְהוָה | דִּבֵּר׃ | |
| -እና-ትቆረጣለች | -እና-ትወድቃለች | -እና-ይቆረጣል | -ያን-ሸክም | የ- | -በ-እሷ-ላይ | ስለ | እግዚአብሔር | ተናገረ | |
| H1438 | H5307 | H3772 | | | | | H3068 | H1696 | |

ס
ס

> በዚያ ቀን፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፥ በታመነው ስፍራ የተከለው ችንካር ይወልቃል ተሰብሮም ይወድቃል፥ በእርሱም ላይ የተሰቀለው ሸክም ይጠፋል እግዚአብሔር ተናግሮአልና።